


SUSTAINABLE LALIBELA

# የፕሮጀክት ቅርበት

ጥገና
ዕሴት መጨመር
አቅም ግንባታ







ላሊበላን የሚያገናኙ መንገዶች

## ዘላቂው የላሊበላ ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀችት የላሊበላን ቅርስ የመጠገን ፣ መንከባከብ እና ቅርሱ ላይ እሴት መጨመር በሚል መርህ የፍራንኮ-ኢትዮጵያ ትብብር ፕሮግራም አካል ነው ። ይህ ፕሮጀክት በፈረንሣይ የልማት ባንክ (AFD) የገንዘብ ድጋፍ፣ በፈረንሣይ የኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል (ሲኤፍኢኢ) እና በፈረንሣይ ብሔራዊ ሳይንሳዊ ምርምር ማዕከል (ሲ ኤን አር ኤስ) ተግባራዊ የሚሆን ነው። በቅርሱ ላይ የሚደረግን አስቸኮይ ጥገና ጨምሮ ለኢትዮጵያን ተማሪዎች እና ለሙያተኞች የሥልጠና መርሃግብርን ያካተተ ስራ ሲሆን በቅርስ አያያዝ ላይ የአቅም ግንባታ ስራና የቅርስ አስተዳደር ስልጠናንም ተግባራዊ ያደርጋል።



የላሊበላ ስነምህዳር

# ርዕሰ አንቀፅ

## ካሊበካን በዘላቂነት እንዴት?

በላሊበላ ለ12 ተከታትይ ዓመታት ጥናትና ምርምር ስናደርግ ቆይተናል፡፡ በመሆኑም ለቅርሱና በቦታው ሂደታዊ ለውጥ ውስጥ አስተዋጽኦ ያደረጉትን የማህበረሰብ ክፍል እንዲሁም የቅርሱን መገኛ ስፍራ በተሻለ መንገድ መረዳት እንድንችል አድርጎናል፡፡ የላሊበላን-ማስቀጠል ፕሮጀክት ለእኛ ለተመራማሪዎች የተለየ እድል ነው፡፡ በተለይ የላሊበላን ማህበረሰብ ከስፍራው በመሆን በጥልቀት ከመረዳት አንፃር፤ ከኢትዮጵያውያን የሥራ ባልደረቦቻችን ጋር በአንድነት ለመስራትን እና ቅርሱን በዘላቂነት ጠብቆ ለማቆየት እና ለመንከባከብ የሚያስችል የተለየ አጋጣሚ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡



### ምርምር:

የጥናትና ምርምር ስራው ለረጅም ጊዜ በጥምር-ሙያተኞች (ኢትዩጵያዊያንና አለም-አቀፍ ቡድን) አማካኝነት ሲካሄድ በመቆየቱ፤ ለፕሮጀክቱ ራሱን የቻለ የጥናት ዘዴ አበርክቷል፡፡ በዚህም መሰረት የመስክ ቅኝትን፣ መረጃ መተንተን፣ እንዲሁም መረጃ ማሳወቅንና መከታተልን ያካትታል፡፡

### ጥምር-ሙያተኞቹ:

ከተለያዩ የሞያ ዘርፍ የተውጣጡ ባለሞያዎች ሲሆኑ፤ የታሪክ ተመራማሪዎች፣ የስነ ቁፋሮ ባለሙያዎች፣ የአለት (ድንጋይ ጥገና) ጠራቢ እና የስነ-ምድር ባለሙያዎችን በአንድነት በመያዝ የላሊበላ ከተማን ጥልቅነት፣ ስብጥርነት እና ሂደታዊ ለውጥ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው ዘደ ስራ የገቡት፡፡



### የአቅም-ግንባታ:

ፕሮጀክቱ ለኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ልዩ ሙያዊ ክህሎት እንዲላበሱ አስተዋጾ የጎላ ሲሆን የተለያዩ ስልጠናዎችን ና የመስክ ልምምዶችን በማበርከት ሃገር በቀል ዕውቀትን በማአጉላት የስፍራውን የቅርስ ጥበቃ እና እንክብካቤ ማሳደግ እና ተጭማሪ እሴትን ለመፍጠር ያስችላል፡፡

### አሳታፊነት:

የላሊበላ ማህበረሰብ ለፕሮጀክቱ መልካም ጅማሮ እንዲሁም በጎ ፍጻሜ ሊኖረው የሚያስችለው የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳታፊነት ሲታካልበት ነው፡፡ ይህም ሲባል ፕሮጀክቱ የታሰብለትን ግብ እንዲመታ ቀጣይነት ያለው ውይይት ማድረግ፣የልምድ ልውውጥን ማካሄድ ና በትምህርት የታገዘ ስረኣት በመፍጠር ተመልካችነትን ወይም ጠባቂነትን በማቆም ዘላቂ ተግባራትን ማከናወን  ይቻላል ብለን እናምናለን።

ማሪ ብሪዶኖ እና ማሪሎር ድራ
የሳይንሳዊ ምርምር አስተባባሪዎች

# አውድ

## የካሊበካ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት – አስጸናፊ ቅርስ



### ላሊበላ፣ ከመካከለኛው ዘመን አንስቶ የረጅም የለውጥ ሂደቶችን አስተናግዶዋል።

በተራራማው የሰሜን ኢትዮጵያ አምብርት ላይ የሚገኘው የላሊበላ ከተማ የአስራአንዱ ውቅር አብያተክርስቲያናት መገኛ ነው፡፡ አብያተ ክርስቲያናቱን በማሳነፅም ሆነ በማነጹ ቅዱስ ንጉስ ላሊበላ ቀዳሚ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ትውፊት እንደተጻፈው፣ ከ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀመሮ ንጉስ ላሊበላ የክርስትና ስርው መንግስት ውስጥ የበላይ መሪ ሆነው አገልግለዋል። ከለተ ዕረፍታቸው በኋላ ቅዱስ ስፍራው (የቦታው ስም) እንደተቀየረና ስሙም ላሊበላ እንደተባለ ታሪክ ያስርዳል፡፡ ይህ ሥፍራ ለረጅም ጊዜ ልዩ ልዩ ክስተቶችን ያስተናገደና የዚህም ውጤት ነው። ይህም ከ13ኛው ክፍለ ዘመን በፊትና ከዛ በኃላ ያላቁዋረጠ ክዋኔ መሆኑን አመላከች ግኝቶችን በምርምር ማየት ተችሎል። ይህን ለመረዳት ከብዙ ዘመን ክራሞት (የቆይታ) ና ጥናት በምነሳት የዛን ዘመን ክስተት አዲስ የአርኪዮሎጂ ስርኣትን በመዘርጋት የቀደመውን በመከለስ የተከናወነ ሲሆን በተደጋጋሚ በሚከሰተው የአየር ጠባይ ለውጥ የላይኛው የአለቱ ክፍል የዝናብ መሸርሸር ፣ ለጽሃይና ንፋስ መጋለጥ ቀድሞ የነበረውን ውብ ይዘት እንዲያጣ ወይም እንዲቀይር ያደረገው መሆኑን መገንዘብና ማወቅ ተችሎል።



### የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት እምብርት ላሊበላ

ላሊበላ ዳግማዊ ኢየሩሳሌምን እንዲሆን ተብሎ በኢትዮጲያዊያን ለኢትዮጵያውያን የተሰራ ቅዱስ ስፍራ ሲሆን የቅዱስ ስፍራዋን (እየሩሳሊምን) ስያሜ ተጋርቷል፡፡ እንደ ሃይማኖታዊ ትውፊቱ አገላለጽ፤ ንጉስ ቅዱስ ላሊበላ ራሱ የተቀበረው በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን፣ የቅዱስ ስፍራው ጎልጎታ እና በሁዋላም ቅዱስ የሆነው ንጉስ ላሊበላ የቀብር ስፍራ በአንድ ላይ መገኘት ላሊበላን ታላቅ የመንፈሳዊ ስፍራ ማዕከል አድርጎታል፡፡ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ለኦርቶዶክሳውያን ዛሬም ድረስ በአፍሪካ ጎልተው ከሚታዩ ቅዱሳን ስፍራዎች መካከለ አንዱ ሲሆኑ አብያተ ክርስቲያናቱ በየ አመቱ በታህሳስ ወር መጨረሻ ለሚከበረው የኢየሱስ ክርስቶስ ና የቅዱስ ላሊበላን ልደት ለማክበር የሚመጡን በመቶ ሸወች የሚቆጠሩ ምዕመናን የሚያስተናግድ ታላቅ ስፍራ አድርጎታል፡፡



## አደጋ የተጋረጠበት ህያው ቅርስ ላሊበላ

ይህ ደማቅ ቅርስና የሃይማኖት ማዕከል በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና ባህል ማዕከል (ዩኔስኮ) በአለም ቅርስነት እ.ኤ.አ. በ1978 የተመዘገበ ቢሆንም ለረጅም ጊዜ ለአደጋ ተጋልጦ ቆይቶል፡፡ ለዚህም በዋነኛነት የዝናብና ጽሃይ መፈራረቅ አለቱ በከፍተኛ ደረጃ እንዲሸረሸር እና ለአደጋ ተጋላጭ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንስቶ አብያተክርስትያናቱን ከአደጋ ለማዳን የተለያዩ ጥገናዎች እና አድሳት ሲደረግላቸው እንደነበር የታሪክ መዛግብት ይመሰክራሉ፡፡ ከተደረጉት የተለያዩ የጥገና ሙከራዎችና ጥናት በመነሳት የአለት ጥገና ሂደትን በመምረጥ የአለት ጥገና ሊደረግ የሚገባ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ እ.አ.አ. ከ1980ዎቹ ጀምሮ ቅርሶቹን ከዝናብ ለመከላከል ልዩ ልዩ የመጠለያ ስራ ሲሰራላቸው መኖሩ ይታወቃል፡፡ በ21ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የቆርቆሮው ጣራ ተነስቶ በዘመናዊ መጠለያ እንዲቀየርም ተደረገ፡፡ መጠለያው የተሻለ አማራጭ እንዲሆን በሚል የመፍትሄ ሃሳብ ተደርጎ ቢዘጋጅም ለረጅም ጊዜ መቆየት እንዲችል ወይም በቅርሱ ላይ አንዳች አደጋ እንዳያደርስ ተብሎ የተከወነ ተግባር አልነበረም፡፡

የላሊበላን አብያተክርስቲያናት መጠበቅ ለእምነቱ ተከታዮች የቀን ከቀን ሃይማኖታዊ ተግባራትን ለመፈጸም ፣ የሃይማኖታዊ ጉዞዎችን ለማስኬድ ፣ የጎብኝዎችን ጉዞ ከማሳለጡም በላይ የቤተክርስቲያናቱ መታደስ የቦታውን የቀደመ ክብሩን መልሶ እንዲጎናፀፍ ያስችለዋል፡፡ ይህንን ለማሳካትም በአሁኑ ሰዓት የአካባቢው ማህበረሰብ፣ የቤተክርስቲያኑ የበላይ ሃላፊዎችና እና የኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

## ላሊበላ–የሚኖርበት ቅርስ



በአመት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተሳላሚ ወደ ቦታው የሚጎርፍ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ነዋሪ ህዝበክርስቲያኑ እለት ተእለት የሚከወንን ሃይማኖታዊ ክዋኔን በአብያተክርስቴያናቱ ያለማቆረጥ ይፈጥማል። የህ ቅዱስ ስፍራ ከ1000 በላይ በሚሆኑ ካህናትና ዲያቆናት ሃይማኖታዊ አገልግሎትን ሳይታክቱ ይሰጡበታል፡፡ አብያተክርስቲያኑ የላሊበላን እና የአካባቢው ምእመናን ብቻ ሳይሆን ለገና ለሰኔ ሚኪኤል ከመለው ኢትዮጵያ የሚመጡ ምዕመናንና ለማንኛውም አይነት ሃይማኖታዊ ሥርዓት እና ክብረ በዓላትን ያለማቋረጥ እሚያስተናግዱ ናቸው፣ ከዚህ ጎን ለጎን ይህ ቅዱስ ስፍራ በውስጡ ከ54000 በላይ የሚሆኑ ነዋሪዎችን ይዞል፣ ይህን ሁሉ ተግባራት የሚያስተናገደው የላሊበላ ከተማ፣ከመሰርተልማት አንጣር ሲታይ እዚህ ግባ የሚባል ስራ አልተሰራም። በቀላሉ የተቆራረጠውን የከተማውን ክፍል የሚያገናኝ መንገድ፣ ለኖሪውም ሆነ ለጎብኝ የሚሆን መጸዳጃ፣ የመንገድ ላይ መብራት፣ የውስጥ ለውስጥ መንገድ በውል ያልትደራጀ ከመሆኑ በላይ የከተማው ፕላን ለዚህ ቦታ ተመጣጣኝ አለመሆኑ እጅግ ያሳስባል። በአብዛንኛው አብያተክርስቲያናቱ ቅጥር ሰፍረው ይኖሩ የነበሩ የአካባቢው ኖሪወች ቀስ በቀስ በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች አማካኝነት ከክልላቸውና ከቦታው ርቀው እንዲሰፍሩ የተደርገ ሲሆን እነዚህ የማህበርሰብ ክፊሎች ያልተደላደል አሰፋፈርና ያሉበት ቦታ ከሚውዱት ቅርስ ጋር እሚያገናኝ ትራንስፖረት አለመኖር ኑሮቸውን አክብዶታል። ከዚህ በተጨማሪ ይህ የተለቀቀ የቅርስ ክልል ለተሳላሚወችም ሆነ ለህዝበ ከርስቲያኑ ምቹ ሆኖ እንዲያገለገል ክልሉን ማስትካከልና የማስዋብ ሰራ ይጠበቃል።

**1 ሰዓት**
ባውሮፕላን ከአዲስ አበባ ያለው
የጉዞ ርቀት
በየብስ አንድ ቀን ተኩል ይሆናል

**54,000**
የነዋሪው ህዝብ ብዛት



**11** ቤተ - ክርስቲያን ብዛት

**50,000+**
የውጭ ሃገር ጎብኚዎች በዓመት ከኮቪድ ወረርሽኝ በፊት
- ሃይማኖታዊ ተጎዡ 200,000 በላይ ይሆናል

# የላሊበላን-ማስቀጠል ፕሮጀክት

እ.አ.አ. በማርች 2019 በኢትዮጵያ እና በፈረንሳይ መንግስት መካከል በተፈረመ የጋራ  ስምምነት የላሊበላን አብያተ ክርስቲያናትን መጠበቅ፣ መንከባከብ፣ ቅርሱን ማልማትና ማሳደግን ማዕከል ያደረገ ሲሆን የሁለቱ ሃገራት የባህል ጥበቃ ና ቅርስ ስምምነት ነው። የገንዘብ እገዛ የሚደረግለት በፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ቢሮ (MEAE)፣ በፈረንሳይ ዴቨሎፐመንት ኤጅንሲ (AFD) እና በብሔራዊ የሳይንስ ጥናት ማዕከል (CNRS) መሆኑ ይታወቃል። የላሊበላን-ማስቀጠል ፕሮጀክት በበላይነት የሚመራው በአዲስ አበባ የሚገኘው የፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል (CFEE) ና በፈርንሳይ ሐገር ይሚገኘው ብሂራዊ ምርምር ማዕከል በጋራ በምሆን ነው፡ ፡ ይህ የላሊበላን-ማስቀጠል ፕሮጀክት አጠቃላይ የላሊበላ ፕሮግራም (መርሃ ግብር) አካል ሲሆን በውስጡ የሚያካትታቸውም የዲጂታል አውደ-ርዕይ፤ የአርኪዮቪዥን ላብራቶሪ (CNRS)፣ ዓለም አቀፍ የቅርስ ጥገና ስትራቴጂ እና የዘላቂ ቅርስ ጥበቃና ቅድመ ጥገና ስራን ለማከናወን እንዲያስችል ተደርጎ የተቀርጸ ነው።

## ላሊበላን–በዘላቂነት ማስቀጠል በፈረንሳይ እና ኢትዮጵያ ቅርስህን አጽን ፕሮጀክት ስር ተመሰረተ

## ላሊበላ ፕሮጀክት

### የዲጂታል አውደ ርዕይ

ላሊበላ ዕምነት ወ ውቅር የፎቶግራፍና ቪድዮ ምስሎችን በመጠቀም ዘመናዊና ተለምዶአዊ ግብዓትን በማጣመር ሲኖግራፍ በተባለዉ የማስኅብኛ መላ በመታገዝ አካታች የሆነ ጥበባዊ ተግዋዥ ዓውደ-ርዕይ ነው። በዓውደ-ርዕዩ ከስፍራው ታሪካዊ፣ አጠቃላይ የአካባቢው ሁኔታ እና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በማዋሃድ በምናብ መሂድ። የዲጂታል አውደ-ርዕዩም በላሊበላ፣ አዲስ አበባና ፈረንሳይ ይቀርባል።

### አለም-አቀፍ የቅርስ ጥገና፣ ጥበቃ እና እንክብካቤ ፕሮጀክት

ይህ በፈረንሳይና ኢትዪጵያውያን የልዩ ሙያትኞች ቡዱን የሚከናወን ሲሆን በሁለት የቅድመ ትግበራ ጥናት መነሻነት መሰረት ያደረገ ነው።

የአለቱን ምንነት እና ጠባዩን በዝርዝር አጥንቶ በመተንተን የጥበቃና እንክብካቤ መፍትዎችን ማበጀት። አሁን ላይ ያለውን መጠለያ ጥንካሬ በዝርዝር ጥናት ማድረግ እና ተለዋጭ የመጠለያ አማራጭ መስጠት። እንዲሁም የመዋቅርና የመጠለያው ወጥ ግምት በግልፅ አብያተክርስቴያናቱ ላይ የሚታይ ሁኔታ ማጥናት ያካትታል።

### ላሊበላን ለዘለቄታ ማስቀጠል ፕሮጀክት

ቅድሚያ የሚሰጣቸውና ባሳሳቢ ሁኔታ ላይ የሚገኙ በ22 የተመረጡ ቦታዎች ላይ የጥገና ስራ መስራት
በቅርስ ጥበቃ፣ጥገና እና ቅርስ አስተዳደር ዙሪያ ስልጠና መስጠት
የስፍራውን ታሪክ እና መስህብነት ከፍ ማድረግ
የዲጂታል መረጃ ማዕከል ማቋቋም
በጉዳት ላይ የሚገኙ የስእልና ምስል ጥገና ማካሄድ
የኢሊክትሪክና ድምጽ መሳሪወችን መግጠም
ዲዛይን መስራት
የወለል ንጣፎችን ማስተካከል
ዋና ዋና ተግባሮች ይሆናሉ

SUSTAINABLE LALIBELA

# ካሊበካ በዞካቂና በቀጣይነት ጉዞ



በስልጠናው ላይ የቅርስ ጥበቃውን፣ የቅርስ እንክብካቤ እና የቅርስ ደረጃን አጠባበቅ በማካተት ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎቸና ባለሙያዎች ፕሮጀክቱ በቅርስ ጥናትና አስተዳደር ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት በሌሎቸ የቅርስ ቦታዎችም ተግባራዊ እንዲሆን ያስችለዋል። ፕሮጀክቱ ቀዳሚ ተግባሩ ኢትዮጵያውያን ከባህል፤ ከቅርስ እና ቱሪዝም አንጻር ቅድሚያ የሚሰጡትን ጉዳይ በመደገፍ ማህበራዊ ተሳትፎን አካታች እንዲሆን ያደርጋል።

በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል (CFEE) አስተባባሪነት፤ የላሊበላ አጠቃላይ ፕሮጀክት፤ የረጅም ጊዜ ልምድ ባለቤት በሆኑት በብሔራዊ የሳይንስ ጥናት ማዕከል (CNRS) እና የፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል (CFEE) በመተማመን እና ከARCCH ጋረ በመጣመር ሳይንሳዊ ምርምሩን (በታሪክ፣ በአርኪኦሎጂ ቁፋሮ፣ ስነ-ህንፃ እና ማህበራዊ ሳይንስ) እ.አ.አ. ከ2009 ጀምሮ ሲመራ ቆይቷል። እነዚህ ምርምሮችም የተለያዩ የአብያተክርስቲያናቱ የቁፋሮ ሂደቶችን፣ የቅርስ አጠባበቅ ታሪካዊ ሂደቱን እና በሚዳሰሱ እና በማይዳሰሱ ቅርሶች ዙሪያ አጉልቶ መስራቱን ያሳያል።

በዚህ የማይቋረጥ የኢትዮጵያና የፈረንሳይ ግንኙነት ከሰራተኛው፤ ከተማሪው እና ከላሊበላ ማህበረሰብ አባላት ጋር የጥምረት ግንኙነትን ከመፍጠር ባሻገር ከኢትዮጵያውያን አጋሮቻችን ጋር ጠንካራ ግንኙንት እንዲኖር ያበረታታል። ይህም በሰጥቶ መቀበል ወይም የዕውቀት ሽግግር እና በጠንካራ ስምምነት ላይ የተመሰረተ ሲሆን በእያንዳንዱ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ተግባር ሂደት ውስጥ የስፍራውን የልዩ ልዩ ምርምር ና የእውቀት ምንጭ ሲያደርግ ሁሌም ሃይማኖታዊ ክዋኒውና ስርአቱን በማክበርና ሚናው የጎላ እንዲሆን በማድረግ ነው።



ክፍል 1



## የአብያተክርስቲያናቱ አስቸኳይ ጥገና ስራዎች

22 ጥገናዎቸን ማከናወን ና ሁለት ተጨማሪ (የመብራት ዝርጋታና ና ወለልን ማስትካከል) ተግባራት፡፡
ለ 20 የዕደ-ጥበብ ባለሙያዎቸ የመስክ ላይ የቅርስ ጥገና ስልጠና በመስጠት ና ወደስራ መስገባት፡፡

# የፕሮጀክ
# መግለጫ

ክፍል 2



## ለስዕልና ቅርፃ ቅርፅ ጥገና ስራዎች

በቤተ-ማሪያም እና መርቆሪዎስ ቤተ-ክህነት በሚገኙ ስዕሎች ዙሪያ መለስተኛ ጥገና ማከናወን፡፡
ለስዕሎች ስለሚደረጉ ዘላቂ ጥበቃ እና እንክብካቤ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፡፡

ክፍል 3



## በቅርስ አስተዳደር ዙሪያ የአቅም ግንባታን ለመጨመር

ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎችና ባለሙያዎቸ በቅርስ ጥበቃና አስተዳደር ዙሪያ ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል ስርዓተ-ትምህርት ማዘጋጀት፡፡
ከፍተኛ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ተማሪዎች ወደ ፈረንሳይ በመሄድ በዩኒቨርስቲ ወይም በማሰልጠኛ ተቋም የመማር ዕድል ማቅረብና ማመቻቸት፡፡

ቶ ዝርዝር
ክፍሎች

NABLE

BELA

ክፍል
4



## የላሊበላን ታሪካዊ እና መስህባዊ እሴቶችን በአርኪዮሎጂ ለማሳደግ

የፍራንኮ - ኢትዮጵያ  በዘርፈ - ብዙ ባለሙያዎች በሚያካትት ቡደን የአርኪዮለጅ ስራዎች ይሰራሉ፡፡
ለተማሪዎች በአርኪዮሎጂ ስራ ዙሪያ የመስክ ስልጠና መስጠት፡፡
ለ50 የቱሪስት አስጎብኝዎች ለጎብኝ መስህብ የሆኑ ስፍራዎችን ማሳወቅ እና ማሰልጠን፡፡

ክፍል
5



## በላሊበላ ለኢትዮጵያውያን ተደራሽ የሚሆን የዲጂታል መረጃ ማዕከል ማቋቋም

የተለያዩ የዲጂታል ቁሳቁሶችን እና መሳሪያዎች ግዢ መፈፀም፡፡
የተለያዩ ስነ - ጥበባዊ ስራዎችን እና 300 የሚሆኑ ያልታተሙ መዛግብትን ና መጽሃፍትን ወደ ዲጂታል በመቀየር የመረጃ ቋት ማቋቋም፡፡
በነዋሪዎቹ አማካኝነት በላሊበላ ዙሪያ የተለያየ ቃለ መጠይቅና የፊልም ስራን መስራትንና ትዝታወችን ቀርጾ ማስቀመጥ፡፡

# የፕሮጀክቱ ቀጣይነት እና ዘላቂነት

## የአንቷን እና የአምባቸው የስራ ጥምረት



አንቷን ጋሪክ

### ለጥገና መዘጋጀት - አገር-በቀል ዕውቀትን ማሳደግና መጠቀም

አንቷን ጋሪክ የድንጋይ ጠረባ ባለሙያ ነው። አንቷን ትውልደ ፈረንሳዊ ሲሆን በሃገረ በካርናክ "ቤተ-መቅደስ" (CFEETK), ለ16 አመታት የጥገና ስራ ሲሰራ የቆየ የዘርፉ ድንቅ ባለሙያ ነው። ይህ ባለሙያ ዛሬ የፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል (CFEE) ባልደረባ ለመሆን በቅቷል። አንቷን በላሊበላ ቤተ-ክህነቶች ለሚደረጉ የአስቸኳይ ጊዜ የጥገና ስራዎች የበላይ ሃላፊ ነው።



አምባቸው ተገኝ

አምባቸው ተገኝ የተወለደው ከላሊበላ አቅራቢያ በምትገኝ አነስተኛ መንደር ነው። በላሊበላ ከተማ ባለ አንድ ሆቴል ውስጥ ይሰራ ነበር። አምባቸው በቱሪዝም እንቅስቃሴ መቀዝቀዝ የተነሳ ስራውን ያጣ ሲሆን እ.ኤ.አ በኤፕሪል 2021 የአንቷን ረዳት ሆኖ ለጥገና ስራው ተቀጠረ።

### "እንዳችን ከአንዳችን ተማርን የልምድ ልውውጥም አደረግን"

**አምባቸው፦** ከአንቷን ብዙ ነገር ተምሬያለሁ። የስራ እቅድ እና የአሰራር ዘዴን እንዲሁም ከባህል አንፃር ደግሞ ስለፈረንሳይ የተሻለ ግንዛቤ እንዳገኝ አድርጎኛል፡ ፡ በዚህ ከሁሉም የላሊበላን-ማስቀጠል ፕሮጀክት አባላት ጋር የሚደረግ የቡድን ስራ ሲሆን የዚህ ፕሮጀክት አካል በመሆኔ እጅግ ደስተኛ ነኝ።

**አንቷን፦** አምባቸው የምንሰራውን ስራ በቀላሉ መረዳት የሚችል እና ለመማር ዝግጁ የሆነ ፈጣን ሰው ነው። ካርታ እንዴት እንደሚነበብ እና ልኬት እንዴት እንደሚከናወን ከማወቁም በላይ አሁን ደግሞ እንዴት ብረት እንደሚበየድ አውቋል። በእደ-ጥበብ እና ቅርስ ጥበቃ ዙሪያም የተለያዩ ስልጠናዎች ይሰጡታል፤ በስራው ሂደትም በርካታ ነገሮችን ይማራል ። እኔም ደግሞ ከአምባቸው በርካታ ነገሮችን ተምሬያለሁ። በተለይ የአማረኛ ቋንቋን፣ የኢትዮጵያውያንን ባህል እንዲሁም ላሊበላን በተመለከተ ደግሞ ታሪኩንና ህዝቧን በሚገባ እንድገነዘብ አግዞኛል።

### "የስራ አሰራር ዘዴ"

**አንቷን፦** እንደ አንድ ረዳት አምባቸው ትርጉሞችን ይሰራል፣ ይመራል፣ ይወያያል፣ እንዲሁም ችግሮችን ይቀርፋል። ለዚህ ፕሮጀክትም በጣም ጠቃሚ ሰው ነው፡ ፡ አምባቸውና የዕደ-ጥበብ ወንድና ሴት ባለሙያዎች፤ ስለ ብረት አበያየድ ስልጠና ይሰጣቸዋል። በድንጋይና በእንጨትም እንዴት መሰራት እንዳለባቸው ስልጠና ይሰጣቸዋል። በስራ ሂደትም የተሻለ ግንዛቤን ያገኛሉ፡ ፡ ይህም  እንዴት መስመር መሳል እንዳለባቸው፣ እንዴት ካርታ ማንበብ እንዳለባቸው እና የኖራ ስራ እንዴት መሆን እንዳለበት  ከተለያዩ መሣሪያዎች ጋር እንዴት መግባባት እንዳለባቸው ይማራሉ። የዚህ ዕደ ጥበብ ባለሙያ ቡድን ዘርፈ ብዙ ልምድ እንዲቀስሙ ይደረጋል ፣ ይህ የስራና ስልጠና ሂደት ሁልጊዜም ቢሆን የአካባቢ እውቀትን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት። በዚህ መሰረት የእደጥበብ ባለሞያወችና ያሰልጣኞች ግንኙነት እውቀትን የማጋራትና የአካባቢን እወቀት ማጎልበትም ይሆናል።

# ማህበረሰብ አቀፍ አርኪዮሎጅ



የማህበረሰብአዊ አርኪዮሎጂ በፕሮጀክቱ (በአርኪዮሎጅ ቁፋሮ) እና ማህበረሰብ አቀፍ ተግባራት በመፍጠር የመማር ሂደቱን በተቀላጠፈ መንገድ የመምራት ዘዴነው። እ.ኢ.አ ከ1950ዎቹ አንስቶ በላሊበላ የተከወናወኑ ተከታታይ የአርኪዮሎጂ ስራዎች የአካባቢውን ማህበረሰብ ከማሳተፍ አኩዋያ ውስን እንደነበሩ ይታወቃል። በዚህ የፈረንሳይ-ኢትዮጵያ ተልዕኮ አማካኝነት የአርኪዮሎጅ ስራ በድጋሚ የተጀመረው እ.ኤ.አ በ2008 ሲሆን ይህም የተሻለ የውይይት እና የመቀራረብን በር ከፍቷል። እ.ኢ. አ በ2010 ተልዕኮው በመካነ-ቅርስ ቁፋሮ ዙሪያ በቤተ ገብረኢል አካባቢ የተጀመረ ቢሆንም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቁፋሮው ቦታ ስያሚ ሳይታወቅ ቆይቶል። የዚህ ቦታ ስያሚ ጉዳዩ የተነሳው ለሁለተኛ ጊዜ የቁፋሮ ስራ በምንሰራበት ወቅት በስራ ባልደረባችን አማካኝነት ነው። በመጋቢት 2013 ቁፋሮ ስራ ከተሳተፉ ከሰላሳ ሰራተኞች በላይ ጋር ተከታታይነት ያለው የጋራ እና የተናጠል ውይይት በማድረግ ለቁፋሮው አካባቢው ስያሜ ለመስጠት ስምምነት ተደረሰ። ይህም ውይይት የጋራ ተነሳሽነትን እና መግባባትን በመፍጠሩ የአካባቢውን ስነ-ቃል፣ አፈ-ታሪክ እና የቀድሞ ዝናን በትውስታ ለመዘርዘር አስቻለ። በዚህም ሂደት ቀይት ተራራ የሚለው ስያሜ ተመራጭ ሆኖ አግኝተነዋል። ከአካባቢ ትውፊቱ በመነሳት ፤ ቀይት ተራራ የሚለው ስያሜ መነሻ በ12ኛው ክፍለ ዘመን የቦታው ባለይዞታ የነበረችና ቦታውን ለቅዱስ ላሊበላ 40 ጊደር ሊያስገዛ በሚችል ወርቅ ለሸጠችለት ሴት ስም ማስታወሻ እንዲሆን በማለት ነው።

ይህ የማህበረሰብ አቀፍ አርኪዮሎጂ ተልዕኮ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመጣመር የተለያዩ የአካባቢውን ስነቃልና አፈታሪክ በማበረታታት በማጎልበት ፣ የታሪክ ባለቤትነት ግንዛቤን በመፍጠር የእኔነት ስሜት በማሳደር በቀላሉ ወደ ተግባራዊ ስራ እንዲገቡ ለማድረግ ያስችላል። የአካባቢው ማህበረሰብ ሰለ ቦታው ባዳበረው ጥልቅ እውቀት የራሱን ታሪክ መልሶ እንዲያድስ እና የአርኪዮሎጂ ፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን ያስችለዋል። በዚህም የውጪ ሃገር ተመራማሪ ባለሙያዎችን የበላይነት ለመቀነስ ያስችላል። በዚህ ፕሮጀክት ውስጥ የማህበረሰቡን ተገቢ ቦታ እና ሚና ለማረጋገጥ በይበልጥ ይሰራል። ይህም ቀስበቅስ ሃገር በቀል ዕውቀትን ማዳበርና በዚህ ላይ የምርምር ስራ እንድንሰራ ያደርጋል።

- በኪዳነማርያም ወልደጊዮርጊስ አያሌው

# የጹሳለኝ ጹጀኔ ምልከታ

## የመስክ ስልጠና እና የአቅም ግንባታ



ስሜ ደሳለኝ ደጀን ይባላል። የምኖረው በላሊበላ ነው። ለአርኪዮሎጂ ያለኝ ጥልቅ ፍቅር የተጠነሰሰው በልጅነቴ አደርጋቸው ከነበሩት የታሪካዊ ቦታዎች ጉዞ እና በሂደትም በዙሪያዬ ያሉት የባህላዊ ቅርሶችን መገንዘብ ከጀመርኩ ጀምሮ ነው። ይህም በአርኪዮሎጂ እና የቅርስ አስተዳደር የትምህርት ዘርፍ ከአዲግራት ዩኒቨርስቲ እንድመረቅ አስችሎኛል።

በእ.ኤ.አ በኖቬምበር 2020 የድህረ ምረቃ ትምህርቴን በላሊበላ የባህል ተቋም በአርኪዮሎጂ ጀመርኩ። የትግበራ መርሃ ግብሬን ለማጠናቀቅም የመስክ ትምህርት ልምምድ ለመውሰድ በቀይት ተራራ ካለው የፈረንሳይ-ኢትዮጵያ የባለሙያዎች ቡድን ጋር ተቀላቀልኩ። ስልጠናውና ልምምዱ በላሊበላን-ማስቀጠል ፕሮጀክት ማዕቀፍ ውስጥ በመሆን በፈረንሳይ እና በኢትዮጵያውያን መምህራን አማካኝነት ይሰጠኝ ጀመር። ይህም የብረታ ብረት ጥናት፣ የሸክላ ላይ ስዕልንና፣ የቤተክርስቲያ ታሪክን ፣የመልእካምድርና አርኪዮሎጂን እንድገነዘብና እንድረዳ አድርጎኛል። ሮማን ሜንሳን፤ የአርኪዮሎጂው ቡድን ሃላፊ፣ በስነ - ንብብሮሽ ወይም የአለቶችን ንብብሮሽ በጊዜ ሂደት የሚገልጣቸውን አተረጓጎም የታሪካዊ ሂደት እና ህግጋትን እንዴት በእውቀት እንድምንተነትን እንዲሁም የቁፋሮ ሂደቱን አንድ በአንድ እንድገነዘብ ድጋፍ እና ምክር ለግሶኛል።

# አሃዝ

ድጋፍ ምንጮች

አጠቃላይ ድጋፍ




**100+**

**የተቀጠሩ ሰራተኞች**

በእያንዳንዱ የአርኪዮሎጂ
ቡድን ውስጥ፣ አናጺ፣ የጥበቃ
ሰራተኛ፣ ስራ አሳላጭ ይሳተፋሉ

**100**

**ስልጠና የሚወሰዱ**

80 ተማሪዎቸ በቅርስ ጥበቃና
አስተዳደር
20 የእደ-ጥበብ ባለሙያዎች

**50**

**ኤክስፐርት**

አለም-አቀፍ እና የፈረንሳይ
ባለሞያዎች

# የፕሮጀክቱ መርሃ ግብር

## የፕሮጀክቱ ጊዜ - 3 አመት ከግማሽ

ክፍሎች

### 2021 ከ.ኬ.ክ

1. የአብያተከርስቲያናቱ ጥገና
የኤሌክትሪክ ዝርጋታ፣ አወቃቀርና ጥናት
የመሬት የማስተካከል ስራ

2. የቤተ-መዛግብት ባለሙያ ቡድን
ስልጠና
ቅርሱ የተሰራበትን ቁሳቁስና መሣሪያ
ጥናትና ትንታኔ ማዘጋጀት

3. ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች የቅርስ
አስተዳደር ስልጠና መስጠት

4. የአርኪዮሎጂ ስራ ማከናወን ና ለጉብኝት
ክፍት ማድርግ
ለአስጎብኚዎች፣ ለባለሙያዎች እና
ለተማሪዎች የመስክ ስልጠና መስጠት

5. የአይቲ እና ዲጂታል ቁሳቁስ ግዢ
መፈፀም ለባለሞያ ስልጠና መስጠት

### 2022 ከ.ኬ.ክ

2. የአብያተክርስቴያናቱ ቅርፃቅርፅና
ስዕሎች ላይ አስችኮይና ተገቢ ጥገና
ማከናወን

3. ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች የቅርስ
አስተዳደር ስልጠና መስጠት
ጥሩ ውጤት ለሚያመጡ ተማሪዎች
የውጭ ትምህርት እድል በፈረንሣይ
ሃገር በቅድመ እና ድህረ ምረቃ
ፕሮግራም እንዲሁም በተግባር ልምምድ
ዕድልን መስጠት

4. የአርኪዮሎጂ ስራወችን መስራትና
ቦታውን ማበልጸግ
ለአስጎብኚዎች፣ ለባለሙያዎች እና
ለተማሪዎች የመስክ ስልጠና መስጠት

5. የመዛግብት ምዝገባ ሂደቱን ማደራጀት
እና አንድ ወጥ የመረጃ ማዕከል
ማዘጋጀት
በፈረንሳይ በኢትዮጵያ ጥናት
ማዕከል (CNRS) የቤተ-መዛግብት
ባለሙያዎች የሚሰጥ ስልጠና መስጠት

### 2023 ከ.ኬ.ክ

2. የአብያተክርስቴያናቱን
ቅርፃቅርፅና ስዕሎች ላይ ጥገና
ማከናወን

4. አርኪዮሎጂያዊ ተግባር
ማከናወን
ለአስጎብኚዎች፣ ለባለሙያዎች
እና ለተማሪዎች የመስክ
ስልጠና መስጠት
የስፍራውን መስህብነት ከፍ
ከማድረግ አንፃር፤ የህትመት
ስራ መስራት

5. የመዛግብት ምዝገባ ማዋቀርና
ወጥ የሆነ የመረጃ ማዕከል
ማደራጀት
በፈረንሳይ በኢትዮጵያ ጥናት
ማዕከል (CNRS) የቤተ-
መዛግብት ባለሙያዎች የሚሰጥ
ስልጠና

# የፕሮጀክቱ ተሳታፊዎች



## ዶክተር አለባቸው በላይ ብሩ

### መሪ መምህር

ዶክተር በአርኪዖሎጂ የዶክትሪት ድግሬ ይዘዋል። በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ረዳት ፕሮፌሰር ፡ ፡ በመካከለኛው-ዘመን megalithic ውስጥ በታሪካዊ ጥንታዊ ቅርስ ውስጥ ልዩ ፡ ፡ ከ 2018 ጀምሮ በፍራንኮ-ኢትዮጵያዊ ተልዕኮ በላሊበላ ቁፋሮዎች ተካሂደዋል ፡፡ ለላሊበላ ማስተር ተማሪዎች ትኩረት የሚሰጥ መምህር፡፡



## ሃና ስዩም ታደሰ

### የገንዘብ አስተዳደር  ሃላፊ

የበጀት አስተዳዳሪ  ባለሙያ ናችው።በዚህ ሞያ እ.ኤ.አ. ከ 2013 ጀምሮ በፈረንሳይ ጥናት ማዕክለ ውስጥ በሃላፊነት ሰርተዋል፡፡ የበጀት አስተዳደሩን ፣ የፋይናንስ ሪፖርቶችን መርተዋል ፣ የሰው ሀይል እና በገንዘብ አስተዳደር ሰራ የተካኑ ባለሞያ ናቸው። በፕሮጀክቱን በስኬት እንዲመሩ በዚህ ፕሮጀክት የፋይናንስ ሃላፊ ሆነዋል፡፡



## ሮማን ሞንሶ

### የፍራንኮ-ኢትዮጵያ የአርኪኦሎጂ ቁፋሮ ኃለፊ

የአርኪዖሎጂ ባለሙያ እና የጂኦ-አርኪኦሎጂ ባለሙያ ናቸው። ተጓዳኝ የ TRACES ላቦራቶሪ (ቱሉዝ) እና CFEE (CNRS) ውስጥ ይሰራሉ። በላሊበላ ከተማ በተካሄደው የቅርስ ጥናት ቁፋሮ ሥራ ከ 2008 ዓ.ም ጀመሮ እየሰሩ ይገኛሉ።



## አንቷአን ጋሪክ

### የአስቸኳይ ጥገና መርሃ ግብር ኃለፊ

ድንጋይ-ቆራጭኛየድንጋይ ጥገና ባለሞያ ፣ በ CNRS ኢንጂነር ናቸው፡፡ በካርናክ የቤተመንግስት ጥገና መሪ ሆነው የአሥራ ስድስት ዓመታት ልምድ አካብተዋል፡ ፡ አባል “በላሊበላ ውቅር አርኪዮሎጅ ቁፋሮ” ለአስር ዓመታት ያህል፡፡



## ዲያቆን መኮንን ገ/መስቀል አማኑ

### የላሊበላ ቤተክርስቲያን ለፍራንኮ-ኢትዮጵያ ትብብር ፕሮግራም አሳላጭ

የተወለደው በላሊበላ ነው ፡ ፡ በአስተዳደር ተመርቀዋል ፡ ፡ በቅርስ አያያዝ ላይ ልዩ ሥልጠና አግኝተዋል፡፡ የላሊበላ ቤተክርስቲያን አስተዳደር ዓለም አቀፍ ግንኙነት ኃላፊ ናቸው፡፡



## ልዩክ እስፓናሴ

### የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ላሊበላ ዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽን ፕሮጀክት

ለ 3 ባህላዊ ቴክኖሎጅዎች ጥናትና ምርምር እና ለባህላዊ ቅርሶች በማስተዋወቅ የተካነ የምስል ከሰታ መሐንዲስ ፡፡ የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ እና የኤግዚቢሽኑ ቴክኒክ ተቆጣጣሪ፡፡



## ዶክተር ክሌር ቦስክ-ቲሴ

### የስዕል እና የቅርፃ ቅርጽ መልሶ መጠገን  መርሃግብር ሳይንሳዊ አስተባባሪ


የምርምር ባልደረባ (ሲኤንኤስኤስ) እና ሳይንሳዊ አማካሪ (INHA) ፡፡ የጥበብ ታሪክ ተመራማሪ ፣ በኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግሥታት ውስጥ የኪነ-ጥበባት ስልጣኔ (ከ 13 እስከ 19 ኛው ክፍለዘመን) ፡፡ በላሊበላ ውስጥ ታሪካዊ እና የቅርስ ጥናት ተልእኮ አስተባባሪ (እ.ኤ.አ. ከ2008-2019)፡፡



## ኪዳነማርያም ወልደጊዮርጊስ አያሌው

### የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ

የተወለዱት በላሊበላ ከተማ ሲሆን በኢትዮጵያ ጥናትና ቅርስ አስተዳደር የመጀመርያና ሁለተኛ ደግሪ ሰርተዋል ፡፡ በላሊበላ የአርኪዮሎጅ ቁፋሮ  የ 12 ዓመት ልምድ ፣ በላሊበላ የቅርስ ልማት ሥራ የ15 ዓመት አላቸው፡፡



## ፕሮፌሰር ማሪ-ሎር ዴራት

### ሳይንሳዊ አስተባባሪ

በ CNRS የምርምር ዳይሬክተር፣ በመካከለኛው ዘመን ኢትዮጵያ የተካኑ የታሪክ ምሁር ፡፡ በላሊበላ ውስጥ የታሪካዊ እና የቅርስ ጥናት ተልእኮ ተባባሪ (እ.ኤ.አ. 2010 - 2018) እና ከዚያ ዳይሬክተር (ከ 2019 ጀምሮ) በላሊበላ የኣርኪዮሎጅ ቡድን መሪና የዚህ ፕሮጀችት አስትባባሪ ናቸው፡፡



## ዶክተር ማሪ ብሪዶና

### ሳይንሳዊ አስተባባሪ

የማህበረሰብ ጂኦግራፊር ሲሆኑ ፣ ከ 2018 ጀምሮ የ “CFEE” የፈረንሳይ ጥናት ማዕከል በኢትዮጵያ ዳይሬክተር ናቸው፣ ፒኤችዲ መመረቂያ ጽሁፍ “በዓለም አቀፍ ፊት ላሊበላ ፣ የኢትዮጵያ ከተማ” የሚል ሲሆን፣ በፓሪስ-ናንተርሬ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ረዳት ፕሮፌሰር ናቸው ፡፡ የዚህ ፕሮጀችት የሳይንስ አስተባባሪ ናችው።



## ቃልኪዳን ጥሩነህ ተክሌ

### የአስተዳደር ረዳት

ትምህርት በሂሳብ አያያዝ እና በአመራር ተመርቀዋል ፡፡ ለዘላቂ ላሊበላ ፕሮጀክት የአስተዳደርና ፋይናንስ አስተዳደር እንዲሁም የፕሮጀክት ዘግጅት  ረዳት ናቸው፡፡



## ዶ/ር መንግስቱ ጎበዜ

### የኢትዮጵያ ባህል ሚኒስትር ለላላሊበላ አማካሪ

የተወለዱት በላስታ ወረዳ ሲሆን የአርኪኦሎጂ ባለሞያ ናቸው። በላሊበላ ጉዳዮች ላይ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ልዩ አማካሪ ናቸው፡፡



## ዴልፊን ደላማረ

### የህዝብ ግንኙነት ባለሞያ

በዓለም አቀፍ ትብብር ተማሪ (የሶርቦን ዩኒቨርሲቲ) ፡ ፡ የፕሮጀክቱን  የት/ቤት ፕሮግራሞችን የግንኙነት ሃላፊ ና የህዝብ ግንኙነት ባለሞያ፡፡

# የባለድርሻ አካላት እና የገንዘብ ድጋፍ መልክት

## የፈረንሳይ ኤምባሲ

በላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት የቅርስ ጠበቃና እንክብካቤ ሂደት ውስጥ ፈረንሳይ ከኢትዮጵያ ጋር ባላት የረጅም ጊዜ ወዳጅነት አስመስክራለች፡፡ ከፈረንሳይ ሪፑብሊክ ፕሬዝዳንት ኢማኑዌል ማክሮን እና ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ወዳጅነት  የረጅም ጊዜ የነበረን  የባህል ግንኙነት በማንቃቱ፤ ለዘመናት የቆየውን የኢትዮጵያ እና የፈረንሳይ ተመራማሪዎችን ግንኙነት ዳግም አነሳስተዋል፡፡

ዛሬ ይህንን ታሪክ ይዘን ነው  የላሊበላ የቅርስ ጥበቃ/ጥገና ፕሮግራም ላይ ያለነው፡፡ በዚህም መሰረት የሳይንሳዊ ምርምርና ስልጠናዎችን ለቅርሶቹ የደህንነት ጠባቂዎች ኢትዮጵያውያን ተዋናዮች ይህንኑ ታሪክ ማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡ ጥምር ምኞታችን ለመፍጠርም ፕሮጀክቱ የሳይንሳዊ አቀራረብንና የመቀራርብ ወዳጅነትን ከላሊበላ ነዋሪዎችና ከዎኪሎቻችው ጋር አስምሯል፡፡ በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥም ፈረንሳይ ለገባችዉ ቃል በታማኝነት ፀንታ ትቆማለች፡፡ ይህም የምናምንበትን ማሳየት ቀጣዩ ትውልድ በእነዚህ ቅርሶች ጥላ ስር ማደጉን ማረጋገጥና በሂደት የሚያስተላልፋት ትውስታ ነው፡፡ ምክኒያቱም ቅርስ ለፖለቲካዊ ህብረት ፣ለትውልድ ጥምረት ፣ለፅኑ ትውልድ መፍጠር፣ ለግዛት አንድነትና ለህዝቦች እኩልነት የሚያደርገው አስተዋፅ ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡

ይሄን ስራ በታላቅ ስኬት እየመራ ላለው የፈረንሳይ የኢትዮፕጵያ ጥናት ማዕከል እና (CNRS) ቡድን አባላት እንዲሁም ከኢትዮጵያውያን ባልደረቦቻቸው ጋር በፈረንሳይ ዴቨሎፐመንት ኤጀንሲ (AFD) ድጋፍ በማድረግ እና በመተግበር ስላከናወኑት ስራ ለማመስገን እወዳለሁ፡፡

ሬሚ ማሬሾ
የኢትዮጵያ እና የአፍሪካ ህብረት የፈረንሳይ አምባሳደር

AMBASSADE DE FRANCE EN ÉTHIOPIE ET AUPRÈS DE L'UNION AFRICAINE
Liberté Égalité Fraternité

## የፈረንሳይ ልማት ኤጀንሲ (ኤ.ኤፍ.ዲ)

የፈረንሳይ ልማት ኤጀንሲ (ኤ.አፍ.ዲ) በኢትዮጵያ የሚከናወኑ የቅርስ ጥበቃ እና እንክብካቤ ፕሮጀክቶችን በገንዘብ እና በቴክኒክ ይደግፋል፡፡  በዚህም መሰረት ተቋሙ በኖቬምበር 2020 ለዚህ አጓጊ እና የተቀናጀ የላሊበላን-ማስቀጠል ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ እንዲሆን ለCNRS የ3.3 ሚሊዮን ዩሮ ድጋፍ አድርጓል፡፡  ይህ ፕሮጀክት የተቀረፀው የፌደራል፣ የክልሉ እንዲሁም የህያው ቅርሱ የበላይ ጠባቂዎች በተገኙበት ነው፡፡

የፈረንሳይ ልማት ኤጀንሲ (.ኤ.ኤፍ.ዲ) በተለይ በበርካታ  ፕሮጀክት አካላት ዙሪያ የሚያተኩር ሲሆን በትግበራ ትርጓሜዎች፣ በአፈፃፀም እና ሂደት ዙሪያ በኢትዮጵያውያንና ፈረንሳያውያን ተወካዮች የሚደረጉ ተከታታይ ውይይቶችን ተገባራዊ ያደርጋል። የበርካታ ተቋማትን እና ተሳታፊዎች የዘላቂ ልማት ግንባታ እንዲፈጸም ያደርጋል። የሃገር በቀል ዕደ-ጥበብ ባለሙያ፣ የወደፊት አርኪዮሎጂ ስልጡኖች፣ የታሪክ ተመራማሪዎች፣ የቅርስ አስተዳዳሪ እውቀትና ችሎታቸውን ተግባራዊ እንዲሆን ያግዛል።  የኢትዮጵያ የቅርስ ስፍራዎች ፤ ለቦታው እንክብካቤ የሚያደርጉ የአካባቢው አስጎብኝዎች፤ ስለስፍራው ያለውን ግንዛቤ ይሳድጋል። መረጃ ቋት ግንባታ ሂደት ውስጥ ማህበረሰብ እና የተለያዩ ህዝባዊ ተሳትፎዎች  በፕሮጀክት እንዲካተቱ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

የፈረንሳይ ልማት ወኪል (.ኤ.ኤፍ.ዲ) ለኢትዮጵያ መንግስት የድጋፍ እንቅስቃሴውን የጀመረው እ.ኤ.አ ከ1996 ጀምሮ ነው፡፡ ይህም የህዝባዊ ተቋማትን እና የሲቪል ማህበረሰቡ  በተለያየ ዘርፍ እንደ ውሃ፣ ሐይል ዝርጋታ፣ የገጠር ልማት እና ግብርና ላይ የሚሳተፍ ሲሆን ይህም በአጠቅላይ ከ600 ሚ ዩሮ በላይ የገንዘብ ድጋፍ አድርጎል፡፡

ቫለሪ ቴሂዮ
የኤ.ኤፍ.ዲ ካንትሪ ዳይሬክተር

AFD

## የፈረንሳይ ጥናትና ምርምር ተቋም

የፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል በተመራማሪዎቹ፣ በመሃንዲሶቹ (ኢንጂነሮቹ)፣ እና በቴክኒክ ባለሙያዎቹ በላሊበላ መሳተፍ ከጀመረ ከአስር አመታት በላይ ሆኖታል፡፡ ማዕከሉ ይህን የላሊበላን-ማስቀጠል ፕሮጀክት በመደገፉ የሚሰማው ደስታ ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ በፈረንሳይ እና በአዲስ አበባ ከሚገኘው የፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል ጥምር የምርምር ቡድን ተመራማሪዎቹ፣ መሃንዲሶቹ (ኢንጂነሮቹ)፣ እና የቴክኒክ ባለሙያዎቹ አማካኝነት በላሊበላ እየተሰራ ካለው ስራ በተጨማሪ፤ መጠነ ሰፊ የሆነ የሳይንሳዊ ምርምር ጥምረትን በፈረንሳይ ና ኢትዮጵያውያን ባልደረቦች መካከል በተቀናጀ መንገድ ጥምረት ለመፍጠር ያለመ ነው፡፡

የተለያዩ የፕሮጀክቱ ክፍል መሰረታዊ ምርምርን ያጣመረ፣ የተሳትፎ ምርምርን እና የምርምር ወቅት የሚደረግን ስልጠና ስፍራውን መጠበቅ እና መንከባከብ ዓላማ ያደረገ እንዲሁም የማዕከሉን ሳይንሳዊ እና አለምአቀፋዊ ፖሊሲ ከማሳካት አንፃር ነው፡፡ የምርምሩ ቃልኪዳን ቃለ ጉባኤ ከኢትዮጵያውያን የሳይንሳዊ እና የባህል ተቋም ባልደረቦች ጋር በመጣመር ሲሆን የአካባቢውን ማህበረሰብ ያማከለ የተቀናጀ የፅንሰ-ሃሳብ እና የተግባር ስልጠናን ያካተተ ነው፡፡ ይህንንም በዋናነት ወጥ የሆነ ችሎታን እና በሙያው የተካነን ባለሙያ ለማፍራት የሚያስችል ሲሆን በምርምር ሲታገዝ ደግሞ የማህበረሰቡንና የሃገሪቱን ፍላጎት በብቃት ለማሟላት ያስችላል፡፡

ሲልቪ ዴሙርዥ
ረዳትሳይንቲፊክ ማኒጀር
ሲ.ኢ.ን.አር.ኢ.ስ

## የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት

የላሊበላ ደብር ጽህፈት ቤት አስተዳደር በአለም-አቀፍ እና በዘርፈ-ብዙ ባለሙያዎች የሚመራውን የፈረንሳይ ኢትዮጵያን የላሊበላን-ማስቀጠል ቡድን ይህንን የዓለም ቅርስ የሆነውንና ለኛ ኩራት ከመሆን በላይ የህይወታችን መድህን የሆነውን ውቅር አብያተ-ክርስቲያን ለማደስ፣ ለመጠበቅ እና ለመንከባከብ ዓላማ አድርጋችሁ ስለመጣችሁ የተሰማኝን ደስታ ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡ በስራችሁ ሁል ከጎን ሆነን የምናግዝ ሲሆን እናንተም ለተሰጣችሁ ተግባር የታመናችሁ ና የተጋችሁ ትሆኑ ዘንድ አደራ እንላለን።

ቅዱስ ላሊበላ ደብር ጽ/ቤት
መምህር ቆሞስ ጽጌስላሴ መዝገቡ

## የላሊበላ ከተማ አስተዳደር

የላሊበላ ከተማ አስትዳደር ጽ/ቤት ይህ አለም አቀፍ ፕሮጅክት ወደ አካባቢይችን ገብቶ ይህን ሕያው ቅርስ መጠበቅ ፣ መጠገን ና መንከባከብ ለተጨማሪ እሴት እንዲውል ለማድረግ በምትሂዱት ጉዞ ሁሉ አብረን መሆናችንን እይልጻልሁ። በስራ ፈጠራና የአካባቢን እውቀት በማጎልብት ክፍ ያለ የልምድ ልውውጥ ኖሮ የዕውቅት ሽግግሩ ኣዲሱ ትውልድ የኣበቶቹን አደራ ተረክቦ ለመጭው ትውልድ የሚያስትላፍበት ፕሮጀክት ታርጉታላችሁ በሚል እምንት እናንተን ተቀብለን ለትግባራችሁ ደግሞ በተሰጣችሁ ጊዜ ና ሃብት በብልሃት ተጠቀሙበት በማለት አደራ እንላለን።

የላሊብላ ከተማ ኣስትዳደር ከንቲባ

SUSTAINABLE

LALIBELA



## አድራሻ

ዘላቂ ላሊበላ ፕሮጀክት የሕዝብ ግኑኝነት ባለ ሙያ
ኢ.ሜል: sustainable.lalibela@gmail.com
ሞባይል ስልክ ቁ.: +251 904 33 33 88

@sustainablelalibela - ዘላቂ ላሊበላ - በማህበራዊ ድህረገጻችን ይከታተሉን

**ልዩ ምስጋና**

አርቲስት ስዐሊ ተገኘ ይርዳው ለልዩ ስጦታውና ግሩም ሥዕሎቹ እናመሰግናለን።
ግራፊክ ዲዛይነር አዲሲምዕራፍ አበበ ፣ ከቤተ-ሰማይ ክርዬቲቭ ሚዲያ ፣ ለፈጠራ ሥራው እናመሰግናለን።
በመጭረሻም ለሁሉም የዘላቅ ላሊበላ ፕሮጀክት አባላት ለዚህ ስራ ላበረከታችሁት አስተዋጾ ምስጋና ይግባችኋል።